# የጎዳናው ፈላስማ

ከየት ነው የመጣሁ
እንዴትስ ተፈጠርሁ
እኮ ለምን ጉዳይ
ፍዳ የምቀበል ባገር ባደባባይ!
እንደደላው ሁሉ ሆድ የተሸከምሁኝ
እንደዘበናዮች ተስፋን የናፈቅሁኝ::
እፍኝ ጥሬ ያረረብኝ
ወስፋት ማስታገሻ
እርቃን መሸፈኛ
እራፊ የምሻ::
ጎዳና የወደቅሁ
ከዚያም ተባራሪ
ድንጋይ ተንተርሶ
ላስቲክ ለብሶ አዳሪ::

ጊዜ ለሰጣቸው
ህይወት አልጋ ባልጋ ለሆነችላቸው
ይይዙት ይጨብጡት ቅጡ ለጠፋቸው:
ሲበሉ ጠግቤ ሲጠጡ ረክቸ
የነሱን ወዘና ድሎት ተመልክቸ
ሲለብሱ የምደምቅ በደስታ ኗሪ
መስየ የምታይ የኑሮ ተጋሪ::

በልደት ወይ በሞት ስሜ ያልተጻፈ
ትራንስፎርሜሽኑ እኔን ያላቀፈ
ልማታዊ መንግስት አንቅሮ የተፋኝ
ኩሩው ኢትዮጵያዊ አርቆ የገፋኝ
እናት አባት የለኝ ጎዳና ነው ቤቴ
ብርድና ሙቀት ነው
ርሀብና ጥም ነው
ህመምና ስቃይ
የኔ የኑሮ አስታዋሽ
የኔ አንጡራ ሀብቴ::

መንግስት የኔን ጉዳይ ያልያዘ በእቅዱ
ሰዎች እንደወገን
ሊቆረቆሩልኝ ሊያዩኝ ያልፈቀዱ
ለሰው ሰው ያልመሰልሁ ሁሌም ተባራሪ
ጉልበቴን አቅፌ ርሀቡን ችየ ከጎዳና አዳሪ ::
ያልተበደርሁትን እዳ እየከፈልሁኝ
በኑሮ የምቀጣ ሀጢያቴ ሳይገባኝ::

ውየ በማደሬ ተኝቸም ስነሳ
"ተመስገን አምላኬ" ካፌ እማይለየኝ
ከቀን ቀን ቢሰማኝ
ሆዱን የሰጠና እንጀራ የነሳኝ::

ሲሉ ሰማሁና
ሞትም ብርቅ ይሆናል እሱ ከተቆጣ
ሆዴን እየፎከትሁ
ተመስገን እላለሁ የባሰ እንዳይመጣ::
መኖሬን ለረሱ አምላክ: እናት: አባት
አይዞህ ባይ ለሌለኝ ወገንና መንግስት
እስቲ እኔ ለምን ነው
ኢትዮጵያ ሀገሬ
መኖሪያየ ክብሬ
እያልሁ እንድዘምር
ስርአት እንዲኖረኝ ባንዲራ እንዳከብር
ክብረ በአል እንዳደምቅ

አስከሬን እንዳጅብ
ሰልፍ ውጣ የምባለው?
በርሀብና ጥም ነው ህያው ነኝ የምለው:
በቀኑ ሀሩር ነው በሌሊቱ ቁር ነው
መኖሬን የማውቀው::
የጠገበ ጠብደል ሂድ ወዲያ የሚለኝ
ልጆች በአግራሞት የሚመለከቱኝ
ሴቶች በአይን ሙሉ ሊያዩ የማይደፍሩኝ
ያም ያም የሚንቀኝ
ያም ያም የሚፈራኝ
ያም ያም የሚጠላኝ
መንግስት ያገለለኝ ሰው የሚጸየፈኝ::

ሲርበው ሲጠማው
የባህር አንጀቱን ጠኔ ሲያላውሰው
ጤና አጥቶ ከመንገድ ህመም ሲደቁሰው
ጸሀይና ውርጩ ሲፈራረቁበት
ሲል ኩርትም ኩርምት::
ደስታ ለራቀው
ተስፋው ለጨለመ ርዕይ ለሌለው
የሚሆነው ላጣ ኑሮ ላልተመቸው
እናት አባት አገር ለሱ ምኑ ናቸው?

ተመስገን ይለዋል በአምላክ የታደገ
እናት እናት ይላል ጡት ጠብቶ ያደገ::
እኔ ምንድን ልበል!
ጎዳና ተጥየ ከውሻ ጋር ያደግሁ
ችጋር የደቆሰኝ በረሀብ የከሳሁ
ላሂየ ተሟጦ
ጅስሜ የወየበው
ውስጤ ተስፋ ያጣው
ገጼ ፊድ ያረገ
ቀለሜ የዛገው !